# በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ተሳታፊ መሆን

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ በመሆን ልጅዎ በትምህርት እና በሕይወት ስኬታማ ለመሆን እንዲዘጋጅ ያግዙታል። በቤት ውስጥ ከልጅዎ ጋር በአፍመፍቻ ቋንቋዎ ማውራት እና ማንበብ እንደሚቀጥሉ ተሰፋ እናደርጋለን። በቤት ውስጥ በቋንቋዎ መነጋገር ልጅዎ በት/ቤት እንዲማር መሠረት ይሆነዋል። ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋዎችን መናገር የሚችሉ ተመራቂ ወጣቶች ከምረቃ በኋላ የበለጠ እና የተሻለ የሥራ ዕድል ይኖራቸዋል።



# ተጨማሪ መረጃ

በት/ቤትዎ ውስጥ ስለሚገኙ የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃን ከፈለጉ፣ የት/ቤቱ ጽ/ቤት ሰዎች ጥያቄዎችዎን ለመመለስ ዝግጁ ናቸው።

ለተማሪዎ ትክክለኛውን የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራም መምረጥን አስመልክቶ ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎ ወይም ተጨማሪ መረጃ ካስፈለግዎ 720-423-2040 ላይ ይደውሉልን። ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኞቻችን ከተገቢ መልሶች ጋር ሊያገናኙዎት ዝግጁ ናቸው።

## የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) የወላጅ አማራጮች ቪዲዮ
**https://bit.ly/2BnoCzB**

የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) የቀጥታ መስመር
720-423-2040

ድር ጣቢያ
mle.dpsk12.org

*Amharic*



# የDPS የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች

## እንግሊዝኛን በመማር ላይ ላሉ ተማሪዎች

DENVER PUBLIC SCHOOLS

Discover a World of Opportunity™

# ወደ DPS እንኳን ደህና መጡ!



በDPS ተማሪዎቻችን ይዘውልን የሚመጡት ብዙ የቋንቋ እና የባሕል ብዝሃነት ዳራ ት/ቤቶቻችን ያበለጽግልናል ብለን እናምናለን። ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዎች ጋር ተጣምረው ተማሪዎች በትምህርት እና በሕይወት ስኬታማነትን እንዲቀዳጁ የሚያግዙ ሀብቶች ናቸው። የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት ወይም (MLE) ፕሮግራሞቻችን ልጆችዎ እንደ ንባብ፣ ሒሳብ እና ሳይንስ ያሉ ሌሎች ትምህርቶችን እየተማሩ እገረመንገዳቸውንም እንግሊዝኛ እንዲማሩ ለማገዝ በልዩ ሁኔታ የተቀረጹ ፕሮግራሞች ናቸው።

DPS የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ እና ለኮሌጅና ለሥራ ዝግጁ ሆነው እንዲመረቁ አግዘዋል። ወደ መደበኛ የመማሪያ ክፍሎች እስኪዛወሩ ድረስ በየብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራም የቆዩ ተማሪዎች በብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች ጭራሹን ተሳትፈው ከማያውቁ ተማሪዎች የበለጠ የምረቃ ምጣኔ አላቸው።

## የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች ምንድን ናቸው?

የDPS ት/ቤቶች ሁለት ዓይነት የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራሞች አሏቸው፡- ባለሁለት ቋንቋ (ልሳነ-ክልዔ) እና እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ። የDPS ባለሁለት ቋንቋ (ልሳነ-ክልዔ) ፕሮግራሞች የመጀመሪያ ቋንቋቸው ስፓኒሽኛ ለሆኑ ተማሪዎች የተቀረጹ ሲሆኑ ትምህርት በስፓኒሽኛ እና በእንግሊዝኛ ይሰጣሉ። በDPS ውስጥ የሚሰጡት ሁለቱ የልሳነ-ክልዔ ፕሮግራሞች TNLI (የሽግግር አፍ-መፍቻ ቋንቋ ትምህርት) እና ባለሁለት/ንክረት(ኢ.መርዥን) ቋንቋ ናቸው።

እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ፕሮግራሞች ከስፓኒሽኛ ውጭ የሆኑ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች ለሆኑ ተማሪዎች የሚመከሩ ናቸው። እንደ ወላጅነትዎ ለልጅዎ የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ፕሮግራም አገልግሎቶችን በምዝገባ ጊዜ የሚሰጥዎትን የወላጅ መፍቀጃ ቅጽ በመጠቀም ይምረጡ። በት/ቤትዎ የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) አገልግሎቶች የማይገኙ ከሆነ፣ ልጅዎ በብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ዞን ት/ቤት ሊመዘገብ ይችላል። ስለ የብዝኃ-ቋንቋ ትምህርት (MLE) ዞን ት/ቤቶች ተጨማሪ መረጃን የት/ቤትዎ ጽ/ቤት ሊሰጥዎ ይችላል።

## እንግሊዝኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ

በአንድ የእንግሊዝኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ (ESL፣ እንዲሁም ELA-E በመባል ይታወቃል) ፕሮግራም ውስጥ ሁሉም የልጅዎ ትምህርቶች የሚሰጡት በእንግሊዝኛ ነው። በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የሚያስ ተምሩ መምህራን ተማሪዎች ሌሎች እንደ ንባብ፣ ሳይንስ እና ሒሳብ ያሉ ትምህርቶችን እየተማሩ እንግሊዝኛንም እንዲማሩ ለመርዳት የተለየ ሥልጠና ያገኙ ናቸው። ት/ቤቱ የአፍመፍቻ ቋንቋው እርስዎ የሚናገሩት ቋንቋ የሆነ አስጠኚ አማካኝነት በእርስዎ ቋንቋም ተጨማሪ ድጋፍ ሊሰጥ ይችላል።

በተጨማሪም፣ ልጅዎ እንግሊዝኛን መናገርና መጻፍ እንዴት እንደሚችል ጠንካራ መሠረት ሊያስይዝ የሚችል የእንግሊዝኛ ቋንቋ ልማት የተባለ ትምህርት በየቀኑ 45 ደቂቃ የሆነ ክፍለ-ጊዜ ይሰጠዋል።

**የእንግሊዝኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ አገልግሎቶችን ለመምረጥ በወላጅ መፍቀጃ ቅጹ ላይ አማራጭ 2 ን ይምረጡ።**